# አዎ ጎንደር "ሽፍታ" ነው!! እልም ያለ ሽፍታ!!

**(By Zemene Kassie)**

አዎ ጎንደር ሽፍታ ነው። የጠገበ ሲያይ "እምቢበል" የሚል ጥጋበኛ "ዛር" ላዩ ላይ የሰፈረበት "ሽፍታ"።አዎ ከጥንት ጀምሮ ጎንደር ይሼፍታል። እምቢ ይላል። አልገዛም አልጨቆንም ይላል።ሲያከብሩት እንጅ ሲነኩት ያመዋል ጎንደር። እምቢተኛ ጥጋበኛ ሽፍታ ነው ጎንደር።አዎ አርማጭሆም ሽፍታ ነው። እምቢተኛ። ከጥንትም። ዛሬም። ጀግናው ጎንደሬ አርበኛ ቄስ ገሪማ ታፈረ/ ገዳይ ገሪማ ገሪማ ቄሱ ፣የጣሊያን ቦምባርድ ቡል ሲል ጢሱ…./ ጎንደሬ በጋሻው በተሰኘው የአምስት አመቱን የበጌምድር አናብስት ጸረ ጣሊያን አርበኝነታዊ ተጋድሎ በዘከሩበት መጽሃፋቸው በገጽ 31 "የጀብዱ ስራ"በሚል ንኡስ ርእስ ስር እንዲህ ይላሉ"አንድ ስሙ ያልታወቀ ያርማጭሆ ጀግና እንዲህ ይላል"።

"ያለጦር መሪ ያለሰራዊት
ያለጥሩንባ ያለነጋሪት
ሲዋጋ ቆዬ ቀንና ሌሊት።
ሳንጃ ገዳይ ከጠባብ ጎራ
ሽንፋ ገዳይ(ከወዲያ) ቋራ
አንጀት አስጎታች እንደ ጀቢራ"

የአርማጭሆ ልጅ እርሳሱ ጎንደሬ በግፍ፣ በጭቆና እና በኢፍትሃዊነት ላይ ሲዘምት "ዝመት " ብሎ የሚያዘው የጦር መሪ እስኪመጣ ተከታይ ሰራዊት እስኪንጋጋ እንኳን አይጠብቅም።ራሱ መሪ ራሱ ተከታይ ሆኖ ይዘምታል። እምቢ ይላል። ይሼፍታል። ጠላትን አምበርክኮ ገርፎ ያባርራል። ጎንደሬ እንዲህ ነው።

አጼ ቴወድሮስም ሽፍታ ነበር። ያውም ኢትዮጲያን አግብቶ ኢየሩሳሌምን በእጮኝነት የያዘ ባለራእይ "ሽፍታ"።እና እንዲህ እንደኛ የሚያቃጥል ነገር ሲገጥመው "የኢትዮጲያባል የኢየሩሳሌም እጮኛ "ብሎ ፎክሮ ብድግ ይል እና ጠላቶቹን ይጠርግ ነበር።

በዚሁ መጽሃፍ/ጎንደሬ በጋሻው/ ገጽ 67 ላይ "የመረባ ጦርነት"በሚል ንኡስ ርእስ ስር የአንዲት እናት፣ የባሏ እና የልጇ አስገራሚ የጦር ሜዳ ውሎ እንዲህ ተዘግቧል።

"……በዚህ አፈና ጦርነት ዋና ሁነው ሲዋጉ የነበሩት ልጅ አንዳርጌ ደስታ የተከበበው ጦር እናዳያመልጥ በወዲያ ና በወዲህ እየተዘዋወሩ ሲከራከሩ በአዲስ ሃይል ከመጣው ጦር/የጣሊያን ጦር/ በሮምታ ተኩስ ተመትተው ወደቁ።ሚስታቸው ወይዘሮ ከበቡሽ ጡሩንባ እየነፉ በየቦታው እየዘለቁ ያዋጉ ስለነበር ተመትተው የወደቁት ባለቤታቸው ልጅ አንዳርጌ ደስታ መሆናቸውን በተረዱ ጊዜ ሬሳቸውን ጎትተው ከጫካ አግብተው ቅጠል አልብሰው ልጃቸው ዋኘው አንዳርጌ ያባቱን ሞት ሲሰማ እንዳይደነግጥ እና የተከበበው ጦር በር ከፍቶ እንዳይሄድ የሚል ሃሳብ በሴቲቱ ህሌና ስለተቀረጸ ዋኘው አንዳርጌ እየፎከረ በቤልጅግ ጠመንጃ በሚዋጋበት ሄዱና አባትህ በዚያ በኩል ጠላትን አስጨንቆታል፡አንተም በርታ እና ተዋጋ የሰከረ አሳ አያምልጥህ ብለው ወደሌላው በኩል ሲመለሱ እኔ ልጅሽ ከፊትሽ ላይ አሳይሻለሁ አለና ከኮረብታው ላይ ለማምለጥ ከሚታገለው የጠላት ጦር አነጣጥሮ ቢተኩስ አንድ የመቶ አለቃ ማእረግ የተሰጠው የጠላት ወታደር በአፉ ተመትቶ ከኮረብታው እንደተንከባለለ ወርዶ ከታች በወደቀ ጊዜ እናቲቱ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ፎከረዋል፡-

የዋኘው እናት ያንገት አስደፊ
ከአፋፍ ላይ ሆና ጥሩንባ ነፊ
የበህር ልጁ ዋኘው አንዳርጌ
ያባቱን ጠላት ጣለው ከግርጌ
ጠላቱ መስሎ ወዳጅን ነው
ጥይት እንደ እህል ያጎረሰው……

እያሉ ሲፎክሩ የሴቷን ድምጽ ጠላት ሰምቶ በሰፈሩ ሽብር ሞላበት። ነፍሱንም ለማዳን ሲሼሽ አንድ ጓዝ አላነሳም ነበር"።

ጎንደር እንዲህ ነው።ጨቋኝ ገዳይ ሲመጣ ሴቱ ከወንዱ፣እናት ከልጁ ይታጠቃል። ይገጥማል። ያሼንፋል። ለኔ ሽፍትነት ይህ ነው።ያ መንፈስ ያ የነ ራስ አሞራው ውብነህ፡ የነቢትወደድ አዳነ መኮንን፣ ብሬ ዘገዬ፣ ዳኛቼው ተረፈ፣ ይስማው አየለ፣ ብሆና ነጋሽ፣ አያናዬ ቼኮል፣ አየለ ተሰማ፣ ፈለቀ ይመር፣ ባሻ ሰንበቶ፣ ቀኛዝማች ወርቁ ስንቄ፣ ቀኛዝማች ባያብል ደስታ፣ ፊታውራሪ መስፍን ረዳ፣ ቀኛዝማች ጥሩነህ ፈለቀ፣ቀኛዝማች ገታው ዘረፋ፣ ቀኛዝማች ዳኜው ተሰማ፣ሰጠርገው ዋሴ፣ አንዳርጌ ጣሰው፣ ወንድማገኝ ረታ፣ ግራዝማች ከበደ መራ፣ቀኝውዝማች ሞላ መሼሻ፣ቀኛዝማች መስፍን ሃይለማሪያም፣ ባላምባራስ ገሰሰ ረታ፣ ባላምባራስ ጎለንቴ ይማም፣....

ያ የነ ኮ/ል ደመቀ፣ ፍርዱ፣መኣዛው ጌጡ፣ ከፈተው አሰፋ፣ ክብሩ አሰፋ፣ ባዩሽ፣ ይብራ፣ መሳፍንት፣ አረጋ፣ ወዘተ መንፈስ ዛሬም በጎንደር ሰማይ ላይ በጎንደሬ ልብ ውስጥ አለ።

ወንድም ብርሃኑ ጁላ ሆይ፡-

አለቆችህም አንተም ወደ ስልጣን መጣችሁ"ንጉሰነገስት" እንድትሆኑ እና እንዲህም እብሪት መናገር ትጀምሩ ዘንድ ክብሪቱን ለኳሹ "ሽፍታው ጎንደር" ነው። ጥንትም ሽፍታ ዛሬም ሽፍታ። እንቢ ባይ የቀትር እባብ። ምንጭንቅ!

ሽፍትነት የምንኮራበት ዛሬም ውስጣችን ያለ እሴት እንጅ የሚያሼማቅቀን ተረት አይደለም። እና ዛሬም፡ ነገም ለወደፊቱም የዘመን ጥጋበኛ እስካለ ድረስ እንሼፍታለን። ሽፍትነት ይለምልም።ክብር ለሽፍቶች!!!